በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን::

# ቅዱስ ጋብቻ

## ክፍል 4

## ንስሐ

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ታህሳስ ፲፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# <u>ምስጢረ ንስሐ</u>

- ንሥሐ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው።

- በቤተ ክርስቲያን ትምህርት፡- ሰው ከተሳሳተ ኹለት ነገሮች ያስፈልጉታል።
  - ሀ. ንስሐ፡- ንስሐ ማለት «ነስሐ» ተጸጸተ፣ ተቆረቆረ፣ ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ነው። በሠሩት የማይገባ ሥራ ወይም ኃጢአት ማዘን፣ ምነው ባልሠራኹት ምነው ባላደረግሁት፣ ምን ቀን ጣለኝ፣ ብሎ መቆጨት ነው። የሚጸጸት ፍጡር ሰው ብቻ ነው ሌሎች ፍጥረታት የመጸጸት ስሜት የላቸውም።

  - ለ. ኑዛዜ፡- /ኃጢአታቸውን የሚናዘዙ እግዚአብሔርን ያስደስታሉ/ ሉቃ 15፣7-10። ኑዛዜ ማለት ደግሞ አንድ ሥራ ከሰራ በኋላ ያንኑ ሳይደብቅ ሳይቀንስ ጨርሶ መናገር ማለት ነው። ንሰሐ ለማንኛውም የጸጸት መግለጫ ይኾናል ኑዛዜም እንደዚኹ ነው ኃጢአትን መናገር ብቻ ሳይኾን ማንኛውም ሰው ሊሞት ሲል ኃብቴን ንብረቴን ለዕገሌ ሰጥቻለሁ ብሎ በቄስ ፊት የሚናገረው የመጨረሻ ንግግር ኑዛዜ ይባላል።

- በቄሱ አድሮ  ኑዛዜውን የሚሰማውና ሥርየትም የሚሰጠው መንፈስቅዱስ ነው።

- በሐዋርያት ጊዜ ከዚያም በኋላ ለረጅም ጊዜ ኑዛዜ በአደባባይ በሕዝብ ፊት ነበር። ለምሣሌ ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን አደባባይ  የሕዝቡን ኑዛዜ ይቀበል ነበር። <u>የሐዋ. ሥራ 19* 18።</u> <u>2ኛ ቆሮ 7*11</u> ። <u>ያዕቆብ 5*16።</u>

# ምስጢረ ንስሐ የቀጠለ…

- የኃጢአትን ሥርየት በምሥጢር የሚፈጽመው መንፈስ ቅዱስ ቢኾንም አገለግሎቱን የሚፈጽሙ ካህናት ናቸው:: ይህም ለሐዋርያት ጌታ በማስተማር ዘመኑ #በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይኾናል፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይኾናል; በማለት በሰጠው ሥልጣን የሚፈጸም ነው:: ማቴ 16*19:: ዮሐ 20*21:: የሐዋ. 5*1-11:: 8*20-22:: 13*8-12::

- የምሥጢረ ንሥሐ አፈጻጸም ተነሳሒው በፈጸመው የማይገባ ሥራ ተጸጽቶ ለወደፊቱ ወደዚህ ክፉ ሥራ አልመለስም ብሎ ወስኖ በፍጹም እምነትና በክርስቲያናዊ ተስፋ ተሞልቶ ማለት የተስፋ ስንቁን ቋጥሮ ወደ ቄሱ ይገሰግሳል የስራውንም ጥፋት አንድ ሳይቀር በቄሱ ፊት ይናዘዛል:: ቄሱም በተሰጠው ሥልጣን በትምህርት በቀኖና ሥርየተ ኃጢአትን ይሰጠዋል ቀኖናውን ከፈጸመ በኋላ ሥርየተ ኃጢአትን ያገኛል ወደ ቀድሞው ክርስቲያናዊ ክብሩ ይመለሳል::

# ምስጢረ ንስሐ የቀጠለ...

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ማንኛውም ምዕመን ከአጥቢያው ቄሶች ውስጥ መምህረ ንሥሐ መርጦ ይይዛል።

- ይህም የነፍስ አባት ይባላል። ቄሱ ለምዕመኑ የነፍስ አባት፣ የንስሐ አባት፣ መምህረ ንስሐ ይባላል። ምዕመኑም ለቄሱ የነፍስ ልጅ፣ የንስሐ ልጅ ይባላል።

- ቄሱ በመከራም ኾነ በደስታ ጊዜ ከነፍስ ልጆቹ ጥፋታቸውን የሚናዘዙት በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት በምሥጢር በግል ነው። አሁን ግን ከጊዜ ብዛትና ከትምህርትም ማነስ የተነሳ አንዳንድ ምዕመናን ሲወልዱ ለማጥመቅ፣ ሲሞቱ ለፍታት ካልኾነ በቀር ኃጢአትን በየጊዜው ለመናዘዝና ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት ወደ ቄሱ የሚሔድ የለም።
- መስቀል ተሳልሞ «ይፍቱኝ» ማለት ሞልቷል ታዲያ ምዕመኑ ከኃጢአት ማሠሪያ የሚፈታው ኃጢአቱን ተናግሮ ቄሱ በቤተ ክርስቲያን በየሚሰጠውን ቀኖና ሲፈጽም ነው። ከዚህም ጋር የኑዛዜ ጉዳይ በቤተ ክርስቲያናችን እየተረሳ ስለሔደ ብዙ ሰዎች በዓመት አንድ ቀን «የስቅለተ ዓርብ» የሚጠበጠቡትንና የሚናዘዙትን ይመስላቸዋል።

## ምስጢረ ንስሐ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት

- በምሥራቅ  መለካውያን ሥርዓት የምዕመናንን ኑዛዜ ለመስማት የሚችሉት ከኤጲስ ቆጶሳት ልዩ ፈቃድ ያላቸው ቄሶች ብቻ ናቸው፤ ምእመናኑም የወደዱትን ቄስ መርጠው የነፍስ አባት ለማድረግ አይችሉም፤ -

- ምሥጢረ ንስሐ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም አለ:: ኑዛዜ በየጊዜው ነው:: ነገር ግን ቀኖና አሰጣጡ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ነው:: ተናዛዡ ሀብታም ከኾነ ቀኖናውን በገንዘብ ይዋጀዋል

- በፕሮቴስታንት ዓለም ደግሞ የቀሳውስትን የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ስለማይቀበሉ የንሰሐንና የኑዛዜን ምሥጢርነትም አያውቁም፤ ተሳስተናል ወይም እንሳሳታለን ማለት በእነሱ ዘንድ ሩቅ ነው::

- መጽሐፋችን «በፍትሐ መንፈሳዊ» «ፈውስ መንፈሳዊ» የተባሉ የስሕተቱን ጠባይና ቀኖናውንም አቀናብረው የሚናገሩ መጻሕፍት አሉን፤

ይቀጥላል...

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።